# ግብፅ የጀመረችው ዓሳ ጉርጎራ ያዋጣት ይሆን?

ኢዛና ዘመንፌስ 03/06/14

ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ላይ ለምትገነባው ታላቁ የህዳሴ ግድብ የመሰረት ድንጋይ ከተጣለ የፊታችን መጋቢት 24 ቀን 3ኛ ዓመቱን ይደፍናል። የግድቡ የግንባታ ሒደት ከተጀመረ አንስቶ የተደረገው ርብርብ የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ይህችን ሀገር  ከድህነት ለማላቀቅ በእርግጥም ቆርጠው መነሳታቸውን በግልፅ ያሳየ ነው ።

ባለፉት 3 ዓመታት ውስጥ ለአንድም ቀን እንኳን ተስተጓጉሎ የማያውቀው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ አሁን የሚገኝበትን እውነታ በተመለከተ የፕሮጀክቱ ዋና ስራ አስኪያጅ ኢንጂነር ስመኘው በቀለ ሲገልፁ፣ “ከአጠቃላይ ዕቅዳችን በትንሹ ሰላሳ ከመቶ ያህሉን ሰርተን ጨርሰናል። እንዲያውም እውነቱን ለመናገር በግድብ ስራ የምህንድስና ሕግ መሰረት እንደቁልፍ ተግባራት ተደርገው የሚቆጠሩትን የግንባታ ሒደቶች ከሞላ ጎደል በማገባደድ ላይ ነን ማለት ይቻላል።” ብለዋል።

አጠቃላይ የግንባታው ሂደት ሲጠናቀቅ ስድስት ሺህ ሜጋዋት የኤሌክትሪክ ሃይል የማመንጨት አቅም እንደሚኖረው  የተነገረለት ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ፣ በዚህ ዓይነት የተፋጠነ ርብርብ ወደ ፍፃሜ እየተረማመደ ይገኛል። በፍጥነት ፍፃሜ እንዲያገኝ ያደረገው ዋነኛ ምክንያት ደግሞ ፕሮጀክቱ ለመላው የሀገራችን ህዝቦች የዘመናት ቁጭት ምላሽ የሚሰጥ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ፣ ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታው መፃኢ ተስፋችን ብሩህ ስለመሆኑ ከወዲሁ የሚያመለክት በመሆኑ ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ  የጋራ ግንዛቤ አለው። ለዚህ ሀቅ ማስረጃ ማቅረብ ካስፈለገም ሌላ ሌላውን ጉዳይ ትተን ግድቡ በታላቁ የዓባይ ወንዝ ውሃ ላይ እንደሚገነባ ያበሰረን መልካም ዜና መሰማቱን ተከትሎ መላው የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ለተከታታይ ሳምንታት ባለማቋረጥ ከአራቱም የሃገሪቱ ማዕዘናት አደባባይ እየወጡ ልባዊ ደስታቸውን ሲገልፁ የተስተዋለበትን ታሪካዊ ክስተት ማስታወስ ብቻ በቂ ይመስለኛል።

እንደኔ እምነት መንግስት ባልተጠበቀ ሁኔታ ድንገት ብድግ ብሎ ይህን ያህል ግዙፍ የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብ በዓባይ ወንዝ ላይ ሊገነባ መወሰኑን ይፋ ሲያደርግ ዜናው በመላ ሀገሪቱ የቀሰቀሰውን የህዝብ ማዕበል የማየት ዕድል የገጠመው ማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር፣ እኛ ኢትዮጵያውያን እንደህብረተሰብ ስንቆጭበት የኖርነውን የጋራ ጉዳይ የምናስፈፅምበት ታሪካዊ አጋጣሚ የመፈጠሩን እውነታ መረዳቱና ግድቡን የግድቡን ግንባታ ዳር ከማድረስ የሚገታን ምድራዊ ሃይል ሊኖር እንደማይችል አምኖ መቀበሉ ሳይታለም የተፈታ ነው። በዚህ ረገድ ከአገር ቤት እስከ ባህር ማዶ የተስተዋለውን የኢትዮጵያውያን የልማት ንቅናቄ፣ በቅጡ መታዘብ ለቻለ ሰው የቁጭታችን ስፋትና ጥልቀት ከምን የመነጨ እንደሆነ ይገነዘባል።

የግንባታው መጀመር በይፋ መበሰሩን ተከትሎ ሥራው የተጀመረው ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ኤሌትክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግድብ የመገንባት ሃላፊነት የተረከቡት ሰራተኞች እነሆ የተለየ ትጋት በሚጠይቅ የቁርጠኝነት መንፈስ የተሰማሩበትን ሀገራዊ ተልዕኮ ዳር ለማድረስ ሌት ተቀን በመስራት ላይ ናቸው። በተለይም ይህ አሁን ያለንበት 2006 ዓ/ም ከገባ ወዲህ ወደ ስፍራው ተጉዘው የህዳሴውን ግድብ የግንባታ ሂደት የጎበኙ ወገኖች የሚስማሙበት ጉዳይ ቢኖር፣ በኢንጂነር ስመኘው በቀለ በዋና ስራ አስኪያጅነት የሚመራው የፕሮጀክቱ አጠቃላይ እንቅስቃሴ እጅግ በሚያስገርም ርብርብ ተጧጡፎ ከመቀጠሉ የተነሳ እነርሱ አስቀድመው ከገመቱት በላይ የደስታ ስሜት እንደፈጠረባቸውና ይህን እውነታ የሚቀለብስ ቀርቶ ለአንድ ቀን ጀምበር መግታት የሚቻለው ኃይል ይገኛል ብሎ ማመንም እንደሚያዳግት ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ የግብፅ መንግስት ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ላይ የምትገነባውን የህዳሴ ግድብ ለማስቆም ያለመ ዓለም አቀፋዊ ድጋፍ የማሰባሰብ እንቅስቃሴ መጀመሩን አንዳንድ መገናኛ ብዙሃን ዘግበዋል። ሰሞኑን ለዚሁ ጉዳይ ወደ አውሮፓ እንዳቀኑ የተነገረላቸው የግብፅ የውሃ ሀብት ሚኒስቴር፣ የጉብኝታቸው ዋነኛ ዓላማ የአውሮፓ ህብረትን ጨምሮ የተለያዩ የምዕራቡ ዓለም ሃያላን መንግስታትን በጉዳዩ ዙሪያ ለማነጋገርና ከተቻለም ኢትዮጵያ የህዳሴውን ግድብ ከመገንባት እንድትታቀብ ያደርጉላቸው ዘንድ ለመማፀን እንደሆነ ዘገባዎቹ አመልክተዋል።

የግብፅ የውሃ ሀብት ሚኒስቴር የአቤቱታ ዘመቻቸውን የጀመሩት በጣሊያን ነበር። የዚህ ምክንያት ምክንያት ደግሞ የህዳሴውን ግድብ ለመገንባት ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር

የኮንትራት የተፈራረመው “ሳሊኒ” ኮንስትራክሽን ንብረትነቱ የጣሊያናውያን ባለሀብቶች ስለሆነ ነው ተብሏል።

ይህ የግብጽ የተቃውሞ እንቅስቃሴ በተለይም የተባበሩት መንግስታት በፀጥታው ምክር ቤት አማካኝነት “ለግብፅ ህዝብ ዘላቂ ህልውና አሳሳቢ አደጋ ሆኖ አግኝተነዋል” የሚሉትን የህዳሴ ግድብ ኢትዮጵያ  ከመገንባት የምትታቀብበትን አስገዳጅ ውሳኔ እንዲወስን ለማድረግ ሲባል የሚካሄድ ዓለም አቀፋዊ የዲፕሎማሲ ጥረት እንደሆነ ነው የተነገረው፡፡ ሀገራችን ለግድቡ ግንባታ የሚውል ምንም ዓይነት የውጭ ድጋፍ እንዳታገኝ ለማድረግ ጭምርም ጭምር ነው፡፡

የግብፅ መንግስት አሁን በጀመረው ይፋዊ አቤቱታ የማቅረብ እንቅስቃሴ ከዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የሚሻው ድጋፍ፣ የናይል ተፋሰስ ሀገራት በፍትሃዊ የውሃ ሀብት ክፍፍል ላይ ለተመሰረተ የጋራ ተጠቃሚነታቸው ሲሉ መክረው ዘክረው የተስማሙበትን የትብብር ማዕቀፍ ውድቅ የሚያደርግና እነርሱ (ግብፆች) እንደከዚህ ቀደሙ በብቸኝነት ተቆጣጥረው የሚፈልጡ የሚቆርጡበትን የቅኝ ግዛት ዘመን የውሃ ድርሻ ውል ለማስቀጠል የሚያስችላቸውን ጫና በኢትዮጵያ ላይ የመፍጠር ጣልቃ ገብነትን ነው።

እንግዲህ ጉዳዩን ከዚህ አኳያ  ስንቃኘው፣ የምናገኘው ተጨባጭ ሀቅ በእርግጥም ግብፆች ከታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብ ግንባታ ጋር በተያያዘ እንኳንስ ዓለም አቀፍ አቤቱታ ለማቅረብ የሚያስገድዳቸው መሰረታዊ ችግርና እነርሱን ከሱዳን በተለየ ሊያሳስባቸው የሚችል ምንም ዓይነት ጉዳት የማያስከትልባቸው መሆኑን ያወቁታል። አካሄዳቸው  “እሳ ጎረጓሪ ዘንዶ ያወጣል” እንዲሉ ያለታሰበ አላስፈላጊ ሁሜታን ሊፈጥር ይችላል፡፡

በያዝነው ዓመት ታህሳስ ወር ውስጥ ኢትዮጵያ፣ ግብፅና ሱዳን ካርቱም ውስጥ ባካሄዱት የሶስትዮሽ ውይይት ኢትዮጵያና ሱዳን ተመሳሳይ አቋም በመያዝ የድምፅ የበላየነት አግኝተዋል። በውይይቱ ላይ የተሳተፉት የግብፅ ተወካይ “በህዳሴው ግድብ የግንባታ ሂደት ዙሪያ  አዲስ ጥናት የሚያደርግ ዓለም አቀፋዊ የባለሙያዎች ፓናል መቅጠር ያስፈልጋል” የሚል ሃሳብ አቅርበው፣  ኢትዮጵያና ሱዳን ሳይቀበሉት እንደቀሩ ይታወሳል።

ይህ ውይይት ኢትዮጵያ ሱዳንና ግብፅ የግድቡ ግንባታ ሊያስከትል የሚችለው አሉታዊ ተፅእኖ ካለ በጋራ ለመስራት የነበረውን ጅምር ያሳያል፡፡ ግብፅ ውይይቱ እንዳይቀጥል

ግትር አቋም ይዛ እስካሁን ባለው ሁኔታ ይውይይቱ ተቋርጧል። ኢትዮጵያና ሱዳን ግን መግባባት ላይ ደርሰው ግብፅን ወደ ውይይቱ መመለስ በመጠባበቅ ላይ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በግብፅ በኩል አሁንም ድርስ የሚስተዋለው ግልፅነት የጎደለውና ሆን ተብሎ የሚደረግ ጉዳዩን የማጓተት እንቅስቃሴ እልባት እስካልተበጀለት ድረስ የምክክር መድረኩ የሶስትዮሽ ሆኖ የሚቀጥልበት ዕድል ሊጠብ ይችላል።

ሰሞኑን ከወደ ካይሮ የተደመጠው ዜና የሚያመለክተውም ግብፆች ዛሬ እንኳን የአባይን ወሃ ለተፋሰሱ ሀገራት ህዝቦች የጋራ ተጠቃሚነት እንዲውል ፍቃደኞች አለመሆናቸውን የሚያመለክት ነው።

ግብፅ ከጥቁር አፍሪካ ሀገራት አንዷ እንደመሆኗ መጠን ብሔራዊ ጥቅሞቿ የሚረጋገጡት ከመላው አፍሪካውያን ህዝቦች ጋር የሚያስተሳስራትን የህልውና ቁርኝነት ከልብ አምና ስትቀበልና ለአፍሪካዊ ወንድማማችነት ተገቢ ክብር ሲኖራት ነው፡፡ ግብፆች ዛሬ እንኳን ካረጀ ካፈጀው የዜሮ ድምር አስተሳሰብ ተላቅቀው በህዳሴው ዘመን አፍሪካዊ ወንድማማችነት የተሰናዳውን የጋራ ስምምነት ማዕቀፍ ለመቀበል መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡

የኡጋንዳው ፕሬዚዳንት ዩዌሪ ሙሴቬኒ ባለፈው 2005 ዓ/ም ግንቦት ወር ላይ የአባይ ውሃ በግዚያዊነት አቅጣጫውን እንዲቀይር ሲደረግ፣ አንዳንድ የግብፅ ፖለቲከኞች ለጦርነት የሚጋብዝ ዛቻ መሰንዘራቸውን ተከትሎ የተናገሩትን ማስታወስ ተገቢ ይመስለኛል። ፕሬዚዳንት ሙሴቬኒ ያኔ ጉዳዩን አስመልክተው ለሀገራቸው ቴሌቪዥን በሰጡት አስያየት "ግብፅ የያዘችው አቋምና የምታነሳው ጥያቄ ከጥቁር አፍሪካ ሀገራት የጋራ ፍላጎት ጋር የሚጣረስ መሆን የለበትም። የናይል ተፋሰስ ጉዳይ በጥቁር አፍሪካውያን ህዝቦች ስምምነት የሚወሰን እንጂ አረቦችን ወይም ደግሞ የምዕራቡን መንግስታት የሚመለከት አይደለም። ስለዚህ ግብፅ ይህን ነባራዊ ሁኔታ መቀበል ይኖርበታል….!"ማለታቸው ይታወሳል።

እንዲያም ሆኖ ግን ግብፆች ዛሬም ድረስ የአፍሪካውያን ወንድሞቻቸውን ቀና ሃሳብ ከቁብ የቆጠሩት አይመስሉም። ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ላይ የምትገነባው ታላቁ የህዳሴ ኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብ የሚስተጓጎልበትን ዓለም አቀፍ ተፅእኖ የመፍጠር ዘመቻ እንድትጀምር የሚያደርጋት አሳማኝ ምክንያት የላትም፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያን

የሀገራዊ መገለጫ የሆነውን ግድብ ለመገንባት የማንም ዕርዳታ እንደማንጠብቅና በራሳችን አቅም ብቻ ጀምረን ልንጨርሰው ቃል እንደገባን እንኳንስ የግብፅ መንግስት መላው ዓለም የሚያውቀው እውነት ነው፡፡ ሀቁ ይህ ሆኖ ሳለ ግብፅ ምዕራባውያን ባለፀጋ አገራችን በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ገብተው ይምናደርገውን እንዲወስኑልን የማድረግ ፍላጎት እያሳየች ነው፡፡ ይህ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንኳን አሁን በ21ኛው ክፍለ ዘመን ከመቶ አመት በፊትም ለአውሮፓውያን ቅኝ ገዥዎች ያልተንበረከከ፣ የራሱን ጉዳይ በራሱ እየወሰነ ከጎረቤቶቹና ከተቀረው ዓለም ጋር በሰላም መኖር የሚፈልግ፣ በዚህ ላይ ጠንካራ አቋም ያለው መሆኑን ግብፅ መዘንጋቷን ያመለክታል፡፡ ስለዚህ ልናስታውሳት እንወዳለን፡፡

እንግዲያውስ የህዳሴው ግድብን ጉዳይ በየግዜው እንደ አዲስ አጀንዳ እያነሱ አላስፈላጊ ውዝግብ የመፍጠር ሙከራ ሲያደርጉ ለሚስተዋሉት አንዳንድ የግብፅ ፖለቲኞች “አሳ ጎርጓሪ ዘንዶ ያወጣል . . .” የሚለውን የኢትዮጵያውያን ምሳሌያዊ አነጋገር ላስታወሳቸው እወዳለሁ።

በተረፈ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብ በዓባይ ወንዝ ላይ መገንባቱ ለሁሉም የተፋሰሱ ሀገራት የጋራ ጥቅም ፅኑ መሰረት የሚጥልና የቀጠናውን ዘላቂ እጣ ፈንታም ብሩህ ተስፋ የሚያጎናፅፍ እንጂ በየትኛውም መመዘኛ የግብፅን ህዝብ የሚያሳስብ እንዳልሆነ ልብ ሊባል ይገባል እላለሁ።